# የሃይወይ አርበኛ ኣይነግድም በኛ!!!!

በዌብ ሳይታችሁ ነጭ ወሬ መንዛት፣
ጥሬ ስጋ ጠግቦ ስለ ራበው ማውራት፣
ድሃን ላታበሉ ቄስን ሰልፍ መጥራት፣
በባነዲራ አጊጦ ሻማ ገዝቶ ማብራት፣
ባህር ተሻግሮ ለባእድ ማቅራራት፣
አብሮ ያልጮኸውን አንቆ ማስፋራራት፣
ሰልፍ ዳቦ ላይሆን ሻማ ላይቀርብ እራት፣
ጩኸትን ቆም አድርጎ አገር ገብቶ መስራት፣
ከወገን ጎን ሆኖ መጣር እንጂ ማልማት፡፡
ቁርስ ከቅንጅት ቢተርፍ ለመጋራት፣
ምሳን ከኦ.ኤል.ኤፍ ከሻዕቢያው እራት፣
አዳር ሚስማር ተራ ምርጫውን ለመስራት፣
ሲነጋ ፍንፍኔ ኢትዮጵያን ለመምራት፣
እንደ ትናንትናው ዘር ቆጥሮ ለመኩራት፣
ስድስት ኪሎ ገብቶ ጠግቦ ለማጓራት፣
ቆዳውና ወርቁን ቡናውን ሰጥታችሁ፣
ደቡቡን ምስራቁን በዋስ አስይዛችሁ፣
ለተገንጣይ ሁሉ ቃል ኪዳን ገብታችሁ፣
መንገስ ምን ያደርጋል አገር ከሌላችሁ፣
የኤርትራው ንጉስ ባሻው ሲነዳችሁ፣
ስም እየለጠፈ ቢያሰማራችሁ፣
እንደናንተ ቢሆን እንደ ምኞታችሁ፣
አገር ተበታትኖ ስልጣን በያዛችሁ፡፡
ኤይቲን ስትሪት ሹም ሽረቱ ቀልጦ፣
ለምኞት እንጀራ ማገዶው ተፈልጦ፣
ማየት ተከልክሎ ህዝብ ዓይኑን ገልጦ፣
ማውራት ተመረጠ ምላስ ከእጅ በልጦ፡፡
ቀላውጣችሁ ኑሩ ድከሙ ቢላችሁ፣
የራበው ሞኝ ነው ኤርትራ ገባችሁ፣
የራበው ጎረቤት ተርፎት ላይሰጣችሁ፣
ርቦት ካበደው ቤት ምነው አንኳኳችሁ፣
ተለማኝ መለመን ከሆነ ምርጫችሁ፣
በምላስ መኖር ልብ እየራባችሁ፣
መንገሱን ወዳችሁ ሰላም ካስጠላችሁ፣
እስክስታ መውረዱ ብዙም አይረዳችሁ፣
ስልጣን መጨበጡ እንዲህ ከራባችሁ፣
የወንድ ልጅ ምክር እኔ ልምከራችሁ፣
ሽፍታን በመዋጮ መግዛት አቁማችሁ፣
ህግ ሞርጌጅ የለውም ታገሉ ገብታችሁ፡፡
ተረትን መጠረቅ ጨዋታን ያደምቃል፣
ስብሰባና ዲስኩር አዳራሽ ያሞቃል፣
ሰልፍና መዋጮም ሞቅ ሞቅ ያረጋል፣
ህግና ሰላም ግን ልብ ይጠይቃል፡፡

ከአመዴ